Institute Of African Economic Studies

**The Gebre-Hiwot Economic Thinking.**

**Alemayehu Geda (Addis Ababa University and IAES)**

**IAES Working Paper Serious NO. A05/2011**

Institute of African Economic Studies.
P.o.Box. 100616
Addis Ababa, Ethiopia
Phone: 251-11-553-7181
Fax: 251-11-553-7181
Email: info@iaesafrica.com
Web: http://www.iaesafrica.com/

# IAES Working Paper

**Corresponding Author: Alemayehu Geda at AG112526@gmail.com or AG@iaesafrica.com**

Mission The Institute of African Economic Studies is (IAES) is an autonomous none-governmental research and training institute whose primary mission is to provide quality, research-based, policy advice to the governments, regional and continental organization, development partners and the private sector in order to contribute to achievement of national, regional and continental development goals. It has also a consultancy wing that works based on the commercial code of Ethiopian and licensed from the Ministry of Industry. The Institute contributes to improved public policy making and implementation by:

Conducting objective policy research and analysis; Informing and providing advice during policy-making process; Building capacity of the Governments of Africa to absorb, undertake and analyze public policy; Strengthening working modalities with the Governments of Africa and other stakeholders; and Enhancing government ministries capacity through on-job training in order to effectively support the policy process.

The IAES is therefore a central source of information and research-based advice on a wide range of policy issues.

The IAES Working Paper Series Presents Work in Progress by Research members and Associates of the Institute. The aim is to solicit comments. The views express in the Working Paper are the views of the authors and not necessarily that of the IAES

# የነጋድራስ ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ መሰረታዊ የኢኮኖሚክ አስተሳሰቦች

**(ይህ ጽሁፍ 'የራስ ወርቅ አድማሴ (አርታኢ) "የ ገብረህይወት ስራዎች" በሚል ርእስ በቅርቡ በ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ፕሬስ በሚታተም መፅሃፍ ላይ ታትሞ የሚወጣ ነዉ)**

**ዓለማየሁ ገዳ**[1]

**በአዲስ አባባ የኒቨርሲቲ**

**የኢኮኖሚክስ ትምህርት ክፍል ፕሮፌሰር**

**መስከረም 2005/September 2012**

**e-mail:Ag112526@gmail.com ፣ ድህረ-ገፅ፡ www.Alemayehu.com**

---

## *ነጋድራስ ገብረ ሕይወት*

ነጋድራስ ወንድሜ የምሁራን ቁንጮ

አስቦ ተነስቶ አዉጠንጥኖ አልሞ

ተዉሮ ቀምሮ ከነጭ ሁሉ ቀድሞ

የወገኑ ስቃይ ባጭር ዕነዲያበቃ

መከረ ነገረ ለባለ ስልጣናት

ህዘቡን እነዲያወጡት ከድህነት ጥፋት

ሰሙት ሰሙትና ዕዉነት ቢመስላቸዉ

ቀጠፉት ባጭሩ ምከሩ አሳስቧቸዉ፡፡



***ምምባሳ ታህሰሰ 2002 [Nov 2009]***

---

[1] ይህን ፅሁፍ ሳዘጋጅ የመጀመሪያዉን ረቂቅ ወደ ኮመፐዩተር በመገልበጥ ለረዱኝ ሳምራዊትና አሰቴር ምስጋናዬ የላቀ ነዉ፡፡ ለ ገብ ረሕየወት በተዘጋጀ ስብሰባ ላይ ጓደ,ኛዬና ባልደረባዬ ዓለማየሁ ስዩም የሠጠኝ ዐስተያየት ፅሁፌን ዕንዳሻሽል ረድቶኛል፡፡ የጓደኛ አይሁንብኝና እንደምንጊዜዉ ከለመድኩት እና ከማቀዉ ዉብ ጭንቅላቱ ተጠቅሚያለሁና ምስጋናዬ የላቀ ነዉ፡፡ አመሰግናለሁ ዓሌ.፡፡

# I. መግቢያ

የነጋድራስ ገ/ህይወት ስራዎች ላይ አንድ ሶስት የምርምር ሥራዎች ሰርቼ በምርምር መፅሔቶች ላይ አሳተሜ ነበር፡፡ በቅርቡ ለማስትሬትና ለመጀመሪያ ድግሪ እንዲሆን ባዘጋጀሁት "የአለም አቀፍ ንግድ ትንታኔ" መፅሀፍ ላይም አንዱ ምዕራፍ የሚያተኩረው በገ/ሕይወት ሥራዎች ላይ ነው፡፡ በዚህ አጭር ጽሁፍ በነዚህ የምርምር ጽሁፎች ያሰፈርኩትን የ የነጋድራስ ሃሳቦችን ጠቅለል አርጌ በአማርኛ ለማቀረብ እሞክራለሁ፡፡

ምንም እንኳ የነጋድራስ የመጀመሪያው መፅሃፋቸው "አፄ ሚኒሊክና ኢትዮጵያ" በኢትዮጵያ በነበረው ስርዐት ላይ ጠንከር እና በሰል ያለ ትችት የሥጠ፣ታሪክ ተመራመሪዎች ምን ዓይነት የምርምር አካሄድ መከተል እንዳለባቸው በውብ ቋንቋ ያስገነዘበ[2]፣ እንዲሁም በዚያን ጊዜ የነበረችው ኢትዮጵያ መከተል የነበረባትን የፖሊሲ አቅጣጫ የነደፈ፣ እንዲያውም ፕሮፌሰር ባህሩ ከብዙ ባንዱ መጣጥፋቸው እንዳስረዱን በኋላ ቀዳማዊ ኃይለስላሴ ተግባራዊ ያደረጓቸውን ሃሳቦችን ያፈለቀ ውብ መፅሃፍ ቢሆንም፡ እኔ ግን እንደኢኮኖሚስትነቴ ለኢኮኖሚ ተንታኞች ይበልጥ የሚቀርበውን ሁለተኛው መፅሃፍ፡- 'መንግሥትና የህዝብ አስተዳደር' ላይ አተኩሬለሁ፡፡

በዚህ ሁለተኛው የትወራ ወይም የንድፈ ሃሣብ (theoretical) ስራቸው ነጋድራስ በደቡብ አሜሪካ በ 1950ዎች ተፈጠረ የተባለውን "በመዋቅራዊ ችግሮች ላይ ያተኮረ የኢኮኖሚ አተናተን" (Structural Economics)፣ በተለይ ደግሞ የፕሬብሽንና የፕሮፌሰር ሲንገርን ስራዎች እሳቸው ቀድመው አውቀው በዚህ መፅሀፍ ፅፈውት ነበር፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በፈረንጆች አቆጣጠር በ1970ዎቹ በፈረንሳዩ ፖለቲካል ኢኮኖሚስት አርጌ ኢማኑኤልን እና ታዋቂው የግብፅ ፖለቲካል ኢኮኖሚስት ሳሚር አሚን እንደተተወሩ የሚነገርላቸው "ያደጉና ያላደጉ አገሮች ያልተመጣጠነ ንግድ ሁኔታ ትንተና" በዚህ መፃፋቸው ቀድመው ትወራውን አድርገውት ነበር፡፡ በተመሳሳይም የታዎቂዎች የእንግሊዝ ኢኮኖሚስቶች ፕሮፌሰር ፒጉና ኬንስን ፣ እንዲሁም የፖላንዱን ዕውቅ ኢኖሚስት ፕሮፌሰር ሚካኤል ካልስኪ ስራዎች ቀድመዉ ዐመላክተዉ ነበር፡፡ ሆኖም ባማርኛ ስለፃፉት ይሁን ከአፍሪካ ስለሆኑ እሳቸው ቀድመው የፈለሰፉትን አስተሳሰብ ሌሎች 40 ና 50 ዓመት ዘግይተው ሲያወቁት በኢኮኖሚክሱ አለም ገናና ና ታዋቂ ሆኑበት፡፡ ጠቅለል ባለ መልኩ ሲገለፅ ነጋድራስ በሁለቱ መጻህፍት በተጠቃለሉት ስራዎቻቸዉ "Development Economics" ወይም "የልማት ምጣኔ ሀብታዊ አተናተን"፡ የሚባለውን የምጣኔ ሃብት ሳይንስ አንዱ ክፍልን ከማንም ቀድመው ፈጥረዋል ማለት ነው፡፡ ይህ የምጣኔ ሀብት ሳይንስ ግን ከሁለተኛው የአለም ጦርነት በኋላ በአውሮፓና አሜሪካ ኢኮኖሚስቶች እንደተፈጠረ ነው ዛሬ ብዙ ተመራማሪዎች የሚያዉቁት፡፡እዘህ ላይ ግን ፕሮፌሰር መሳይ ከበደ ስለ ገብረ ሕይወት በፃፉት ፅሁፍ ገብረህይወት ዘመናዊነትን ከአዉሮፓ አንስቶ ኢትዮጵያ ላይ ለመጫን ነበር የሞለከረዉ የሚል

---

2 ገ/ሕይወት የሚደነቁባቸዉ እኚህ የታሪክ መመርመሪያ ሳይንሳዊ አካሄዶች ከ ገብረህይወት በፊት አለቃ ታዬ በፃፉት የ ኢትዮጵያ ታሪክ መፃሃፋቸዉ (ከዛም ላይ ተቆንጥሮ በ 1914 በታተመዉ መፃህፋቸዉ) ጠቅሰዉታል፡፡ እንደዚህም ብለዉ ነበር "...የታሪክ ትምህርት የሚጠቅመዉ ግን እዉነተኛ ታሪክ ሲሆን ነዉ፡፡ እዉነተኛ ታሪክ ለመጻፍ ግን ብዙ መጠንቀቅ ያሻል... ይህንንም ለማድረግ ሰባት የግዚሃብሄር ስጦታ የተባሉ ነገሮች ያስፈልጋሉ እነዚሁም.... እግዚሃብሄርን መፍራት፤አስታወይ ህሊና፤ የ ቋንቋ አገባብ ማወቅ፤የማያዳላ ልቡና፤ትጋት፤ትዕግስት፤መጠንቀቅ.." (አለቃ ታዬ ፤1914፤ <u>የኢተዮጵያ ህዝብ ታሪክ፤ገፅ 24</u>፡፡ አዲስ አበባ፤ሴንትራል ማተሚያ ቤት) ፡፡ ይህ ጥቅስ እንደሚያሳየዉ ገብረ ህይወት አንዳንዶቹን ዐረፍተ ነገሮች ቃል በቃል ነዉ የደገማቸዉ፡፡ ነገሩን ጠቅለልና አጠር ማረጉ ግን ድንቅ ነዉ፡፡በዛ ላይ በጣም አድናቂያቸዉ ነበር፡፡

ድምዳሜ ቢጤ ላይ የመጡ ስለመሰለኝ፤ በኔ ግምት ይህ ሃሳብ ልክ አለመሆኑን በመፃህፉ ብዙ ቦታዎች የተመለከተ መሆኑን (ለምሳሌም በአዲሱ የ አአዩ እትም ገፅ 28 እና 37 ለናሙና መጥቀስ እነደሚቻል) ለመጠቆም እወዳለሁ፡፡ በነዚህ ቦታዎች ገብረ ሕይወት የአዉሮፓን ዕዉቀት በአያሌዉ አድንቀዉ ሲጨርሱ ወዲያዉ አዉሮፓን እንከተል ይላሉ ብለን ስንጠብቅ "ስለዚህ ጃፓንን አጥንተን እንከተል" ነዉ እንጂ አዉሮፓን እንከተል ካለማለታቸዉም በላይ "ደንብ ሁሉ ምንም ቢጠቅም በተለየ ጊዜያት ዉስጥና ለተለየ ህዝብ ብቻ ነዉ" ፤ እንዲሁም "ዕዉቀት ላላቸዉ ህዝቦች ደግ የሆነ ደንብ ዕዉቀት ለሌላቸዉ ሕዝቦች ትልቅ ጉዳት ይሆንባቸዋል" ማለታቸዉን ለመጠቆም እወዳለሁ፡፡ በዛን ጊዜ ምናልባትም ስለባህልና ተመሳሳይ ጉዳዮች ከአትዮጵያ ስልጣኔ ሁኔታ ለመነሳት ቢቻልም ስለኢኮኖሚ እደገት ግን (ክስመት ካልሆነ!) ከኢትዮጵያ ለመነሳት የሚከብድ ይመስለኛል፡፡ ክስመቱን ግን ከኢትዮጵያ ሁኔታ ተነስተዉ፤ቀጥዬ እንደማትተዉ፤ አብራርተዉታል፡፡

እንግዲህ ከዚህ ሁኔታ በመነሣት ነው በዚህ ፅሁፌ የነጋድራስን ኢኮኖሚ ነክ ሥራዎችን አጠር አድርጌ በማቅረብ "የልማት ምጣኔ-ሐብታዊ ትንተና" የሚባለው ትምህርት መሰረቱ አፍሪካ ወይም ደግሞ ኢትዮጵያ መሆኑን መጠቆም የምፈልገው፡፡ በተጨማሪም፡ የነጋድራስ ስራዎች አሁንም ለኢትዮጵያ ችግሮች  መፍትሂ የሚጠቁሙ ቁልፍ ሥራዎች  መሆናቸዉን አስረግጬ ለመግለፅ  እሞክራለሁ፡፡

# II. የ ነጋድራስ ገበረ ሕይወት መሰረታዊ ሃሳቦች

በሚከተሉት ገፆች ውስጥ የነጋድራስን አስተሳሰብ "የነጋድራስ ሞዴል" ብዬ እጠራለሁ፤ በደምሳሳዉ ሞዴል ማለት ወጥ እና አጠር ባለመልኩ የኢኮኖሚ አስተሳሰብ የሚገለጥበት የአስተሳሰብ መሣሪያ ልንለው እንችላለን፡፡ ብዙ ጊዜ ሞዴል የሂሳብ ቀመር መልክ ሊይዝ ይችላል፡፡

ነጋድራስ በ ጀርመን አገር መማራቸዉ ይታወሳል፡፡ ከ ዚህም ጋ ተያይዞ የነጋድራስ ሞዴል በዘመኑ የጀርመን የኢኮኖሚ አስተሳሰብ የተቃኘ ይመስላል፡፡ ይህንንም እንድንል የሚያደርገን በመጻህፉ ዉስጥ የጠቀሰዉ አንድ ሰዉ (ኢኮኖሚስት) ቢኖር ኬሪ የሚባል ብቻ ነዉ፡፡ ይህ ሰዉ በዘመኑ ዝነኛ የነበረዉ ማቲዎስ ኬሪ ወይም ደግሞ ከሱ በላይ ዝነኛ የነበረዉ ልጁ ሄነሪ ኬሪ ይሆናል፡፡ የ ሄነሪን ዝነኛነት ማርክስና ኤንግልስ ሰይቀሩ መስክረዉለታል (የቻንግን መጻሃፍ ይመልከቱ)፡፡ ሄነሪ የ አሜሪካዉ ፕሬዘዳንት ሊንከለን አማካሪ ብቻ ሳይሆን ከነ አባቱ ታዋቂዉ የዘመኑ የ ጀርመን ኢኮኖሚሰት ፊሬድሪክ ሊስት ላይ ከባድ ተጽኖ አሳድርዋል፡፡ ሊስት ጀርመን ማደግ ከፈለገች ለእንግሊዝ ነጻ ገበያ መርህ ሳትበገር ጨቅላ ኢንዱስተሪዎቻን በመንግስት ድጋፍና ከለላ መሳደግ አለባት የሚለዉን አስተሳሰብ ያመጣዉ በነዚህ አሜርካኖች ተጽኖ ይመስላል (ለምሳሌም ሄነሪ የ እንግሊዝ ኢኮኖሚስቶች (በተይ፡የሪካርዶና ሰሚዝን)፤ የነጻ ገበያ ቲዎሪ አሜሪካን ዘላለም የጥሬ ዕቃ አቅራቢ ለማድረግ የተወጠነ የ እነግሊዝ

ኢምፒሪያሊዝም ዘዴ ነዉ ይል ነበር)፡፡ ጠቅለል ባለ መልኩም ሲታይ የ ገበረህይወት የአስተሳሰብ ዘዴ የአዉሮፓን የዕድገጥት ጥበብ ከኛ ሁኔታና ታሪክ አጣጥሞ ማቅረብ ነዉ፡፡ ይህ የኢኮኖሚ ማሳደጊያ ጥበብን ከታሪክ ጋር አቆራኝቶ የማጥናት ዘዴ ደግሞ ሔርመኑቲክ (hermeneutic) የሚባለዉ የዘመኑ የጀርመን ሊቃዉንት (በተለይ ደግሞ ዲቲ ና ዊበር) የሚጠቀሙበትና ከ እንገሊዝ ሊቆች ይለየናል የሚሉት የ ጥናት ዘዴያቸዉ ነዉ (የ ዊበርን የ ፕሮሰታንተ ኤቲክ መጻሃፍ ይመልከቱ)፡፡ የ ገበረህይወት ያጠናን ዘዴ ወይም ሞዴል ከዚህ ጋ በጅጉ ይመሳሰላል[3]፡፡

በነጋድራስ ሞዴል ማንኛውም አገር የመልማት ተስፋ አለው፡፡ ዳሩ ግን ሁለት መሰናክሎች (ተግዳሮቶች) ሊጋረጡበት ይችላሉ፡፡ እነርሱም ግጭት ወይም ጦርነትና የውጪ የንግድ ሚዛን መዛባት ናቸው፡፡ እንግዲህ ለነጋድራስ ያንድ አገር ክስመት ወይም ዕድገት ደረጃ በነዚህ ተግዳሮቶች ግዝፈትና ደካማነት ይወሰናል፡፡ የነጋድራሰን ሀሳብ ከሥሩ ለመረዳት እነዚህን ሁለት ተግዳሮቶች (ዉስጣዊና ውጫዊ አንበላቸው) በጥልቀት መመልከት ይሻል፡፡

## 2.1 ውስጣዊ የልማት ተግዳሮቶች/መሠናክሎች/

በነጋድራስ አስተሳሰብ ጦርነትን ያህል የልማት መሰናክል የለም፡፡ ጦርነት ልማትን በመገደብ ከተፈጥሮ ቁጣም ሆነ ካልተመጣጠነ የውጪ ንግድ ጉዳት ያይላል፡፡ ለነጋድራስ የአገራችንን እድገትን ጠፍንጎ የያዘው ይህ መሠናክል ነው፡፡ ለነጋድራስ የግጭት ወይም ጦርነት መነሻው የአንዳንድ ግለሠቦች ሳይደክሙ የሰውን ላብ የመሻት ፍላጎት ነው፡፡ ያገራችን ገበሬ ደግሞ ተበታትኖ መስፈሩ ለነዚህ ዘራፊዎች ምቹ ተዘራፊ አድርጎታል፡፡ የዚህ አይነቱ አካሄድ ድምር ውጤት ጥቂት ሰዎች ባመረቱት ብዙ ስራ ፈት ዘራፊዎች ተመጋቢ ማድረግ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ሃብት የመፍጠርን አቅም፣ በተለይ በእርሻው ክፍል ኢኮኖሚ፣በዕጅጉ ስለሚያቀጭጭ የልማት ማነቆ ይሆናል፡፡ ለእርሻ ይውል የነበረው የሰው ኃይልም ወደ ሽፍታነቱና ዘራፊነቱ ሲያደላ የልማት ተስፋን የበለጠ ያደበዝዘዋል[4]፡፡

ነጋድራስ ይህችን ጦርነት ነክ ገለፃቸውን በዛው አልገቱትም፡፡ ይልቅም ይህ ግጭትና የግጭት መንስኤን በዛን ጊዜ 'ቋንቋ ነገዶች' (በዛሬ ቋንቋ ብሄረሰቦች) መሃል ምን መልክ እንደሚይዝ ተንትነውታል፡፡ ይህንንም ሲገልፁ ዘረፋና ቅሚያ በእያንዳንዱ ነገድ ውስጥ እንዳለ፤ አንዳንዴ አንድ ነገድ ባንዱ ላይ እንዲነሣ በተለያየ መንገድ የነገዱ ተጠሪ ነን ባዮች እንደሚቀሰቅሱ፡፡ ጦርነት ሲነሳ ሁለቱ ነገዶች እንደሚተላለቁ፤ የነገድ መሪዎች ነን ባዮች ግን ወደ ጦርነት ቦታ ድርሽ እንደማይሉ፤ በአፋቸው ለነገዳቸው በማሰብ ጠበቃ የቆሙ እንደሚመስሉ በተግባር ግን ለግል ጥቅማቸው እንጂ ለነገዱ ደንታ እንደሌላቸውና ድብቅ አላማቸው መዝረፍ እንደሆነ በዚህ መፅሃፍ ውስጥ ፍንትው አርገው አሣይተውናል፡፡ ይህ በነገዶች መሀል የሚነሳ ግጭት መደባዊ መለክ እነዳለዉ ገ/ህይወት በጥናታቸዉ ላይ ያስረገጡት ጉዳይ ነዉ፤፤ እነዲህም ይላሉ

---

3 ኬሪ የታባለዉ ኢኮኖሚስት ይሄ ሳይሆን አይቀርም ብሎ ፍንጭ የሰጠኝ ጋደኛዬ የለንደን ዩኒቨርስቲዉ ፕሮፌሰር ዊክስ ሲሆን፣ የ ቻንግ መጻሀፍ ቀጥሎ ረድቶኛል፡፡በተጨማሪም ስለ ሔርመኑቲክ ዘዴ አየለ ዘዉገ በ 1973 ስለ ገበረ ህይወት በጻፉት መሰከረም መጽሂት ላይ መጥቀሳቸዉ ፍንጭ ሆኖኛል፡፡

4 ጦርነት-ነክ ጥናቶች ገ/ሕይወት እንዳደረጉት የጦርነት አሉታዊ ገፅታ ላይ ብቻ አያተኩሩም፡፡ እንዳዉም ጦርነት አድገትን ሊያመጣ እነደሚችል ይሞግታሉ፡፡ ገ/ሕይወት ይሕንን የ ጦርነት ሌላ ገፅታ ያልተነተኑት ትንታኒያቸዉ በኢትዮጵያ ታሪክ ላይ ስለተመሰረቱ ሳይሆን አይቀረም ፡፡

> ይያንዳንዱ ቆሮ አሳብ መቼም ለመቀማት ነው:: ነገር ግን ይህን እውነተኛ ሀሳባቸውን ሸፍነው ስም ብቻ ለመፈለግ የተነሱ ያስመስሉታል::...ቆሮዎች ግን በመጀመሪያ ለመጋደል አይፈላለጉም ነበር::... ገባሮቻቸውን እያስተራረዱ ቆሮዎቹ እርስ በራሳቸው በፍቅር ለመላላክ አይመለሱም:: (ገጽ 32)

ይህ የገ/ሕይወት የጦርነት ምንስኤ ትንታኔ (ሃቲት) ባለፉት 10 አመታት (እ.ኤ.አ ከ 1999 ጀምሮ) ግጭቶችን ለመተንተን ኢኮኖሚስቶች በተለይ ደግሞ የ ኦክስፎርድ ዩኒቨርሲቲ ፕሮፌሰር የሆኑት ፓዉል ኮሊየር እና አብረዋቸዉ የሚፅፉ ብዙ የምርምር አጋሮቻቸዉ በመስኩ የዘረጉትን *"ስግብግብነትና በደል/የፍትህ ዕጦት (greed and greviance) እነደ ግጭት መንስኤዎች"* የሚባለዉን የግጭቶችና የርስ በርስ ጦርነቶች ሞዴል ገ/ሕይወት ከ 90 ዐመት በፊት ተዉረዉት ነበር ማለት ይቻላል፡፡

በ ገ/ህይወት ሞዴል ዉሰጥ የዚህ ዉጤት በጦርነቱ ምክንያት ገበሬው በብዙ ድካም ካለማው መሬት ተፈናቅሎ በመቆየቱ የለማው መሬት ተበላሽቶ እንደገና "ሀ" ብሎ መሬቱን ማልማት ሲጀምር ምን ያህል ልማትን ወደ ኋላ እንደሚመልስ ማሥረዳታቸው ላይ ነው፡፡ የጦርነቱ አሧሪት በተደገመ ቁጥር  የኋልዮሽ የልማት  ጎዞው ህዝቡን በዛዉ ልክ በድህነት አዙሪት ውስጥ ተደፍቆ እንዲቀር እንደሚያደረግ ነጋድራስ በአንክሮ ገልጸውታል፡፡

> ያንዱን ትንሽ ንጉስ አገር ሌላው እየጠቀለለው ይሄዳል:: በጊዜ ብዛትም ትልልቅ ነገስታት ይወጣሉ:: በውስጣቸውም በግድያና በዘረፋ የበለጠውን እያዩ ራስ ደጃአዝማች እያሉ ይሾማሉ:: የነገሱበትንም አገር ለእነርሱ ያካፍላሉ፣ የቀረው ሁሉ የነዚህን ማዕረግ እያየ ስምና ሹመት አገኛለሁ እያለ በህዝቡ ውስጥ ያለው እያንዳንዱ ሰው በግድያና በዘረፋ እንዲመሰገን ይጥራል:: ጦርነቱም ከድሮ የባሰ ይሆናል::... ጦርነቱን የሚያነሱ ነገስታቱና አለቆቹ ሁሉ ልባቸው ሐብት እንደፈለገ አይገልጹም:: ነገር ግን ስም ለመፈለግና ለማግኘት ወይም ሐይማኖቶችን ላመስፋፋት ወይም የተጠቃውን ለመርዳት አስመስለው ይነሳሉ:: የጦርነቱ ሁሉ ፍጻሜና ምኞት ግን መዝረፍና ማስገበር ነው:: ይህንንም ስላልን እውቀታቸው የሰፋ ንገስታትም ቢሆኑ መዝረፍን አይተዉም:: አዘራረፋቸው ግን  የእውቀት አዘራረፍ ነው:: (ከገጽ 33 እስከ 34)

ይህ እንግዲህ ለነጋድራስ  አንዱና ዋንኛው ውስጣዊ የልማት መሰናክል ነው፡፡ የመሠናክሉ ምንጭ ጦርነት  ሲሆን የጦርነቱ ሰለባ የሚሆነው የዕርሻ ዕድገት ነው፡፡ በጦርነቱ የሚያልቀው የህዝብ ብዛት ከባስልጣኖች የስልጣን አለመረጋጋት ጋር ተደማምሮ ልማትን እንደሚያሽመደምደው   ነጋድራስ ገልፀውታል፡፡ ነጋድራስ የጦርነቱ ውጤት በትናንሽና በትላልቅ ንጉሶች መሃል እንደገና ተጭሮ አገሪቱን ሲያምስ እንደነበረ በግልፅ አስቀምጠውታል፡፡ እነዲያውም ነገሩ በዚህ ከቀጠለ የዕርሻ ልማታችን ከሥሩ ጠፍቶ፤ያየር ንብረታችንኛ የመሬት ለምነት ተናግቶ የልጅ ልጆቻችን ወደ ውጪ አገር እንደሚሰደዱ ተንብያዋል፡- የአሜሪካን  ዲቪና  አረብ አገር ለመሄድ ያለውን ሰልፍ  ልብ ይሏል፡፡ አንዱ

ታመሪዬ፤አማኑኤል፤ ይህንን ደርዝ ይዞ የ2ኛ ዲግሪዉን መመረቂያ ፅሁፍ 4 ኪሎ (አአዩ) ሰርቶበታል፡፡

ነጋድራስ ውስጣዊ የልማት መሰናክሎች ከሚሉት ከላይ ከተጠቀሰው ሀሳብ ጋር አያይዘው መዋለ-ነዋይ (ኢንቨስትመንት)ና የተማረ ወይም የሠለጠነ የሠው ሀይል ለልማት ወሳኝ እንደሆነ ለማሳየት ጥረዋል፡፡ በተጨማሪም  የግብርናው ክፍል ኢኮኖሚ ዕድገት ወሳኝ ቢሆንም የከተማው ክፍለ ኢኮኖሚ ካላደገ ግብርናው ብቻውን ሊያድግ እንደማይችል በጠራ ቋንቋቸው አሳይተዋል፡፡ ለነጋድራስ የከተማው ኢኮኖሚ ለገጠሩ የገበያ ምንጭ ብቻ ሳይሆን የሰለጠነ የሠው ሀይልና የቴክኖሎጂ ዕድገት መሠረትም ነው፡፡ ይህንን የ ገ/ህይወት ዉስጣዊ የልማት መሰናክል አተናተን አቀርቦትና ፍላጎት የተባሉትን የኢኮኖሚክስ ፅንሰ-ሃሳቦች ይዘን እነደሚከተለዉ ልናቀርበዉ እንችላለን፡፡

## 2.1.1 አቀርቦት በ ገ/ሕይወት ሞዴል

ይህ አቃራረብ የሚኪተሉት የነጋድረስ ታሳቢ ሁኔታዎች ላይ የተመረኮዘ ነው፡፡ የመጀመሪያው ታሳቢ ሁኔታቸው ያገሪቱ መሬት ጫካና ገና ያልተነካ/ያልታረሠ መሆኑ፤ ሁለተኛ የህዝብ ዕድገት ለዕርሻ ምርት መጨመር አስፈላጊ መሆኑና በመጨረሻም ጦርነት የህዝብ ቁጥር መቀነሥን እንደሚያስከትል ታሳቢ መረጋቸው ነዉ፡፡ ይህንን ይዘን በነጋድራስ ሞዴል አቅርቦት የሚጨምረዉ የህዝብ ቁጥር ሲጨምር፤የስራ ክፍፍል ሲጠነክር እንዲሁም በምርታማ ስራ ላይ የተሰማራዉ ህዝብ በአንፃራዊነት ሲጨምር ነዉ፡፡ በአንፃሩ ጦርነት ሲያይል አቅርቦት እንደሚቀንስ አድርገው ቀርፀውታል፡፡ይህ ሁኔታ በቀመር [1] ተመልክትዋል፡፡

ም$_1$= የ (ጦ፤ህ፤ክ፤ጉ)    ዉጤት [1]

<u>*መግለጫ*</u>፡  ም$_1$= የእርሻ ምርት ጦ= ጦርነት/ግጭት፤ ህ= ህዝብ ዕድገት፤ ክ= የስራ ክፍፍል፤
ጉ = በምርታማ ስራ የተሰማራ አምራች ሃይል/ጉልበት

በቀመር [1] የተሠጠው የዕርሻ ምርት በገበያ ዋጋ ቢሠላ የሚከተለዉን መልክ ሊይዝ ይችላል፡፡

ም$_1$ በገበያ ዋጋ= ዋ$_1$ም$_1$=የ(ጉ) ዉጤት [2]

ጉ = የ(መ) ዉጤት [3]

ዋመ=የ(ዕዉቀት) ዉጤት [4]

*መግለጫ*: መ= መዋለ ነዋይ (ኢንቨስትመንት) $ዋ_1$= የግበርና ምርቶች ዋጋ፤ ዋ= አገራዊ አጠቃላይ ዋጋ (የግብርና ና ግብርና ያልሆነዉ ክፍለ ኢኮኖሚ አማካይ ዋጋ)፡፡ በተጨማሪም ሁለት ፊደሎች ተከታትለው ሲፃፉ ብዜትን ያሳያሉ፡ ምሳሌ፡- $ዋ_1ም_1$= ($ዋ_1$) x ($ም_1$ )

በቁጥር 2, 3, እና 4 የተሠጡት ቀመሮች የዕርሻ ምርት አቅርቦት እንዴት ዕንደሚወሠን የሚያሣዩ ናቸው፡፡ በገ/ህይወት ሞዴል ወስዋ የዕቃዎች ዋጋ የሚወሠነው ለማምርት የጠፋውን ጉልበት ተንተርሶ ስለሆነ ቀመር (2) ይህንኑ ሁኔታ ያሣያል፡፡ ዕውቀትና አንቨስትመንት አንድን ዕቃ ለማምረት የሚውስደዉን ጊዜ በማሳነስ ብዙ ዕንድናመርት እንደሚረዱን በቀመር 3 እና 4 እንደተመለከተዉ አሳይተውናል፡፡ ይህ አቀራረባቸው በማርክሲስትና በ ዴቪድ ረካርደ የኢኮኖሚ የዋጋ ትመና አተናተን ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ ለገ/ህይወት 4ኛው ቀመር ቁልፍ ነው ፡ ምክንያቱም በዕወቀት ደረጃ ልዩነት ሰዎች ወይም አገሮች ዕቃዎቻቸዉን የሚገበያዩበትን ሚዛን ይወስናልና፡፡ ከዚህ ጋር አያይዘው ገ/ህይወት ያብራሩት ጉዳይ አንድ ምርት ዋጋ አለው የሚባለው ሰዎች አጠቃቀሙን በደንብ ሲያወቁ ጭምር መሆኑን ነው፡፡ ይህ አስተሳሳባቸው ታወቂው የአሜሪካ ኢኮኖሚስት ፓዉል ባረን በ 1957 (እ.ኤ.አ) በፃፉውን የዕርግጠኛና የአንፃራዊ ሃብት ልዩነት አተናተን ጋ ተመሣሣይነት አለው፡፡

## 2.1.2 ፍላጎት በ ገ/ሕይወት ሞዴል

ገ/ሕይወት የኢኮኖሚውን አጠቃላይ የፍላጎት አዝማሚያ ሲገልፁ በዚህ ዘርፍ ዕዉቅ የሆኑትን የሚካኤል ካልስኪ (1933፣ 1971 እ.ኤ.አ) እና ኬንስ (1936 እ.ኤ.አ) መሠረታዊ ሃሳቦች ቀድመው አመላክተዋል፡፡ ይህ ሃተታቸው በኢኮኖሚክስ ትምህርት ዘርፍ ባያሌው የሚታወቀውን የዕርሻና የእንዲስትሪ ክፍለ-ኢኮኖሚ ግንኙነትንም ይነካል፡፡

ለገ/ሕይወት የግብርናዉ ክፍለ ኢኮኖሚ አድጎ አጠቃላይ የፍላጎት ማነስ ችግር ከገጠመዉ በሁለት መልክ ሊፈታ ይችላል፡፡ አንደኛው የግብርና ምርቶች የዋጋ መቀነስና በዚሁም ምክንያት ሸማቾችን በማበረታተት ሲሆን፣ ሁለተኛው የዉጪ ገበያን በማፈላለግ ነው፡፡ የዉጪ ገበያ ማግኘት ግን ሊሣካ የሚችለው ምርታማነትን በዕርሻው ክፍለ-ኢኮኖሚ በመጨመር ነው፡፡ ይህ ደግሞ ቴክኖሎጂን በገጠር ማስፋፋት ግድ ይላል፡፡ እዚህ ላይ ግን ቴክኖሎጂ በገጠር ሲስፋፋ የገበሬው ገቢ በዋጋ መቀነስ ምክንያት ሊቀንስ ዕንደሚችል በ 1950ዎች ፕሬብሽና ሲንገር የተባሉ ምሁራን አመጡ የሚባለዉን ነድፈ-ሀሳብ ቀድመው ገ/ህይወት ተንትነዉት ነበር፡፡

ጠቅለል ባለ መልኩ ሲታይ የገ/ህይወት ሞዴል ሶስት ክፍለ-ኢኮኖሚዎችን ያጠቃላለ ነው ማለት ይቻላል፤ ሆኖም ግን ሞዴላቸው ያተኮረው በዕርሻው ክፍለ-ኢኮኖሚ ላይ ነው፡፡ ከዕርሻ ዉጪ ያለዉ ኢኮኖሚ በሁለት አቅጣጫዎች ዕርሻው ላይ ተፅኖ እንደሚያደርግ አብራርተዋል፡፡ አንደኛው መንገድ ቴክኖሎጂ በማቅረብ ምርታማነትን መጨመሩ ሲሆን ሁለተኛው መንገድ

ለዕርሻ ክፍለ-ኢኮኖሚዉ ገበያ መፍጠሩ ነው፡፡ ይህ አሰተሳሰባቸው በሚከተለው ቀመር ሊጠቃላል ይችላል፡፡

$$ዋ_1ም_1= ዋ_2ም_2+ዋ_3ም_3+ፍ_1+ቀ_1 \qquad [5ሀ]$$

<u>መግለጫ</u>፡ ዋ=ዋጋ፤ ም= ምርት፤ ፍ= ፍጆታ፤ ቀ = የቀረጥ ገቢ፤ 1 = ዕርሻ፤ 2 = ዕርሻ ያልሆነዉ ክፍለ ኢኮኖሚ፤ 3 = ወደ ዉጪ የሚልክ ክፍለ-ኢኮኖሚ፤ በተጨማሪም ሁለት ፊደሎች ተከታትለው ሲፃፍ ብዜትን ያሳያሉ፡ ምሳሌ፡- $ዋ_1ም_1$= ($ዋ_1$) x ($ም_1$ )

በተራ ቁጥር [5ሀ] የተቀመጠው ቀመር የግብርናው ክፍል ኢኮኖሚ አቅርቦት ከዕርሻ ዉጪ የሆነው ክፍለ-ኢኮኖሚ ፍላጎትን፣ የዉጪ ንግድ ፍላጎትን እነደገናም ከራሱ ከግብርና ክፍለ-ኢኪኖሚዉ የሚመጣን የፍጆታ ፍላጎቶች አሟልቶ በተጨማሪም ለመንግስት የቀረጥ ገቢ እንደሚፈጥር ያሣያል፡፡ እንደ ገ/ሕይወት አካሄድ በዚህ ቀመር የሚታየው የፍላጎትና አቅርቦት ሁኔታ ከተዛነፈ የግብርና ምርቶች ዋጋ ከፍና ዝቅ በማለት ሚዛኑ እንዲጠበቅ ያደርጋል፡፡ይህም ሁኔታ በስዕል 1 ጠቅለል ባለ መልኩ ቀርቧል፡፡ስዕሉ የተሰራዉ የግብርናዉ ምርት አቀርቦትና ፍላጎት ከ ገበያዉ የምርቱ ዋጋ ጋር ያለዉ ዝምድና ላይ በማተኮር ነዉ፡፡ ስለሆነም የገበያዉ ዋጋ ሲወጣና ሲወርድ አቅርቦትና ፍላጎት ስዕሉ ላይ በተሰጡት ጠቋሚ መስመሮቻቸዉ ላይ በሚደረግ ቁልቁልና ሽቅብ የመንሸራተት እንቀስቃሴ ይገለፃሉ፡፡ የመንሸራተቱ ብርታት በ መስመሮቹ የተዳፋትነት ሁኔታ ይወሰናል፡፡በአንፃሩ ሌሎች የአቀርቦትና ፍላጎት ወሳኝ ምክንያቶች (ለምሳሌም በቀመር 1 እና 5ሀ የተሰጡት እነደ ጦርነት፤ የህዝብ ዕድገት፤ቀረጥ ወዘተ ያሉት) ሲለወጡ በነፃ ገበያ ዋጋ ና ለገበያ በሚቀርበዉ ተያያዥ ምርት ላይ ያላቸዉ ተፅኖ የሚገለፀዉ የአቀርቦትና የፍላጎት ጠቋሚ መስመሮቻቸዉ አሁን ካረፉበት ቦታ እንደ ተፅኖዉ ሁኔታ ወደ ላየና ወደ ታች ከፍና ዝቅ በማለት ይሆናል፡፡

**ስዕል 1፤ የአቅርቦትና የፍላጎት ሚዛናዊ አካሄድ በ ገ/ሕይወት ሞዴል**




በፍላጎት መሣሣት ወይም ደግሞ በዉጪ ገበያ ተፎካካሪ ለመሆን የግብርና ምርቶች ዋጋ የሚቀንስ ከሆነ፤ ገበሬው የቴክኖሌጅ ተጠቃሚ ለመሆን ገንዘብ ይችግረዋል- ገቢዉ ይቀንሳልና፡፡ በዛ ላይ ነጋዴዎች በመሃል ገብተው የገበሬዉን የገቢ ድርሻ ይሻማሉ፡፡ በዚህ

ሁኔታ የቴክኖሎጂ ተጠቃሚነት በብድር ሊካሄድ ቢችልም በቁጥር 5(ለ) የተሠጠው ቀመር እንደሚያሣየው ገበሬዉ (ብሎም አገሪቱ) የብድር ጫና ይመጣባቸዋል፡፡

ብ= መ+ወ(ብ-1) [5ለ]

<u>መግለጫ</u>፡ ብ= ብድር፤ መ= የመዋለ-ንዋይ ፍሰት (እንቨስትመንት)፤ ወ = ወለድ ብ-1 = እስካሁን ያለ ጠቅላላ የብድር መጠን

ይህ የግብርናዉ ክፍለ-ኢኮኖሚ ብድር እየበዛ ከሄደ አበዳሪዉ ገብሬውን ከመሬቱ በመንቀል መሬት በጥቂቶች ዕጅ እንድትሆን ሊያደርግ እንደሚችል የ ገ/ህይወት ሞዴል ያሣያል፡፡

በቁጥር 5(ሀ) የተሠጠው ቀመር የግብርናውን ክፍለ-ኢኮኖሚ አቅርቦትና ፍላጎት ሚዛን አእንጻሣየን ሁሉ የሚከተለው ቀመር ተመሳሳዩን ሁኔታ በተቀረው ክፍለ-ኢኮኖሚ (2 እነበለዉ) የሣየናል፡፡

ዋ2ም2= ዋመአ+ (ዋ1ም1– ፍ1-ቀ1) [6]

<u>መግለጫ፡ </u>መአ= በአገር ውስጥ ወጪ የተሸፈነ መዋለ-ነዋይ ነው

በቁጥር [6] ቀመር የተመለከተው ከግብርና ወጪ የሆነው ክፍለ-ኢኮኖሚ ለአጠቃላይ ኢኮኖሚው የሚሆን የመዋዕለ ነዋይና የፍጆታ ዕቃዎች አቅራቢ ነዉ፡፡እስካሁን ያየነዉ ይህ አካሄዳቸዉ ከ ማረክሲስት ፖለቲካአል ኢኮኖሚ አቀራረብ ጋር በዕጅጉ ይመሳሰላል፡፡ ከዚህ ክፍለ-ኢኮኖሚ የሚመጠው መዋለ-ነዋይ ወይ በአገር ውስጥ አቅም (መአ) ወይ ከውጪ በሚገኝ ብድር (መዉ) የሚሸፈን ሲሆን በቁጥር [7] የተመለከተውን መልክ ይይዛል፡፡

መ = መአ + መዉ [7]

ቀ = ቀ1 + ቀ2 + ቀቅ [8]

መአ = ቀ [9]

በ ገ/ህይወት ሞዴል ያገር ውስጡ መዋለ-ነዋይ ወጪ ደግሞ የሚሸፈነወ በመንግስት ነዉ፡፡ ይህ ወጪ በቀመር 8 ትና 9 እነደተመለከተዉ በግብርና (ቀ1)፣ ከግብርና ዉጪ በሆነው ክፍለ-

ኢኮኖሚ ($\text{ቀ}_2$) እንዲሁም በቅንጦት ዕቃ ላይ በሚጣል ቀረጥ ($\text{ቀ}_{\text{ቅ}}$) እንደሚሸፈን የገ/ሕይወት ሞዴል ያሣያል፡፡አንድ ላይ ሰብሰብ ብናደርጋቸዉ ከ ቁጥር 7 ዕስከ 9 የተሰጡት ምልከታዎች የሚቀጥለዉን አጠር ያለ፤ ቀመር 7ትን የሚተካ ሌላ ቀመር ይሰጠናል (7ለ እንበለዉ)፣

$$\text{መ} = \text{ቀ} + \text{መ}_{\text{ዉ}} = (\text{ቀ}_1 + \text{ቀ}_2 + \text{ቀ}_{\text{ቅ}}) + \text{መ}_{\text{ዉ}} \qquad \text{7ለ}$$

እዚህ ጋ ከተነሳዉ የ ኢንቨስትመንት ጉዳይ ጋር አያይዘዉ ገ/ህይወት ሌላው ያመላከቱት ጉዳይ በትርፍና በወለድ መካከል ስለሚኖረው ግንኙነት ነዉ፡፡ በ ገ/ሕይወት ሞዴል የትርፍ መጠን ሁሉ ጊዜም ከወለድ መጠን መብለጥ አለበት፡፡ ይህ ካልሆነ በባንክ ገንዘብን ማስቀመጥ ያወጣልና መዋለ ንዋዩን በኢኮኖሚዉ ዉስጥ የሚያፈስ አይኖርም፡፡ ለገ/ህይወት ገበሬዉ ከእንደዚህ ያለው ብድር ሊጠቀም የሚችለው ቅርብና የተሣለጠ የግብይት ሥርአት ኖሮት ትርፉ ከ ወለዱ ከበለጠ ብቻ ነው፡፡

የ ገ/ሕይወት ሞዴል ሌላ ለየት የሚያደርገው ነገር ስትራክቸራሊስት የሚባሉትን ኢኮኖሚስቶችን በመቅደም የተዛባ የገቢ ስርጭት በአጠቃላይ (በማክሮ) ኢኮኖሚወ ላይ ያለውን ተፅኖ በአንክሮ በመግለፁም ጭምር ነው፡፡ ይህንንም እንዲህ ብለዉ ገልፀዉታል፡፡

> በስራ ያልሰለጠኑ ህዝቦች ያልተሰራ ዕቃ ካገራቸዉ አዉጥተዉ ሸጠዉ ትርፍ ብር ቢያገኙ ለጊዜዉ ነዉ እንጂ አያዘልቃቸዉም፡፡መሬታቸዉ በጊዜ አርጅቶ አህል መስጠቱን ሲያቋርጥ የሚሸጡት ነገር ሲጠፋ የልብስ መግዣና ምግብ አጥተዉ እናገኛለን ሲሉ ወደ ሌላ አገር ይሰደዳሉ፡፡…..የሚነግደቡትም ነጋዴዎች ያገሩ ሰዎች ቢሆኑ ያዉ ነዉ፡፡ ባለ መሬቱ እየደኸየ ነጋዴዉ ግን እየተጠቀመ የሂዳል፡፡ማለት ያገሩ ሀብት በጊዜ ብዛት በ ጥቂቶች ሰዎች እጅ ይጠቀለላል፡፡እነዚህም ጥቂቶች ሰዎች የተወለዱበት አገር ብዙ ፍሬ እነደማይሰጥ ሲያዩ የሰበሰቡትን ብርና ወርቅ ይዘዉ በደህና ወደሚኖሩበት አገር ይሂዳሉ፡፡ብዙ ሃብት ያከማቸ ሰዉ በሄደበት አገር ይመቸዋልና ያገር መዉደድን ነገር ከጉዳይ አይቆጥረዉም፡፡ …..የሚበላዉንነና የሚለብሰዉን ያጣ ድሃ ተወለደበትን አገር የሚወድበትን ምክንያት ያጣልና ያገሩ መንግስት ቢበረታ ወይም ቢጠፋ ግድ የለዉም፤ ስለዘሁም መንግስት የሚጠቀምበት ያገሩ ሀብት በጥቂቶች ሰዎች እጅ ሲሰበሰብ አይደለም በመላዉ ህዝቡ እጅ ሲከፋፍለዉ ነዉ እነጂ፡፡ …የሀብታሞች አኗኗርና የሰራተኛው ድሃ አኗኗር አይነቱ እንበል መጠን የሚራራቅበት አገር መንግስቱ ከጥፋት አፋፍ እንደደረሰ ያስረዳል፡፡ የኢትዮጵያንም ህዝብ ሁኔታ ብንመለከት እንደዚሁ ያለ ጥፋት እንዳይደርስ ያስፈራል፡፡ ባንድ ፊት ነግደው የሚያድሩት የውጪ ሀገር ሰዎችና ለህዝቡ አንዳች ጥቅም ሳይሰሩ ድካሙን የሚቀሙ አንዳንድ ሹማምንት ደህና ደህና ቤት እየሰሩ እያጌጡ የተመቸ ኑሮ ሲኖሩ እናያለን፡፡ ባንድ ፊትም የእለት ምግብና ያንድ አመት ልብስ እናገኛለን ሲሉ ብዙ ሺ.ህ ድሆች ወባና ችጋር ፈጅቷቸው ከድሬደዋ አንስቶ እስከ አዲስ አበባ ድረስ ከምድር ባቡር ጎን ለጎን አልፈው አልፈው ተቀብረዋል፡፡ ግማሾቹም የተቀበሩበት መቃብር ጠሊቅ ስላልሆነ ዱሮ አጥንታቸው ወቶ ከምድር ባቡር መንገድ ግራና ቀኝ ተበትኗል፡፡(ገጽ **118-119)**

> … ያማረ የግንብ ቤትና ትንንሽ ጎጆ አጠገብ ላጠገብ ተሰርተው እናያለን። ባንዱ ቤት ውስጥ ትልቁ ጌታ ህዝቡ ደክሞ ያፈራውን ገንዘብ በከንቱ ሲያባክን፣ በጎጆው ውስጥ የሚኖረው ደሃ የሚበላውና የሚለብሰው የሚያበራውም አጥቶ በረሃብና በብርድ ተጨብጦ በኩበት ጢስና በእድፍ ውስጥ ይጨማለቃል። (ገጽ 120)

በዚህ ትንትና ገ/ህይወት አንደ ዕውቁ የፓላንድ ምሁር ሚካኤል ካልስኪ የኢኮኖሚ ተዋናዮችን የሚመለከቷቸዉ በመደባዊ ይዘታቸው ነዉ። እንዚህ ተዋናዮችም በተቋማት ላይ ያላቸውን ተፅዕኖ፤ ተቋማትም እነዲሁ በኢኮኖሚው ላይ ያላቸውን እንድምታ በውሉ አጢነዉታል። በመጨረሻም የነጋድራስ ውስጣዊ የልማት ችግር ያልኩትን ሳጠቃልል እሳቸዉ ያነሷቸውን ሁለት መሰረታዊ ሃሳቦች እንደገና በመጠቆም ነው፤ እነሱም :-

i. የሃብት ክፍፍል በቅጡ አለመመጣጠንና በሃገር ልማትና ሃገር ሉአላዊነት ላይ የሚያመጣውን አሉታዊ ተፅዕኖ ፤
ii. ኢኮኖሚያዊ ትንተናቸው መደባዊ መሆኑና የልማት ተቋማት ወሳኝ ሚና የሚጫወቱ መሆናችን ማሳሰባቸዉ ነው፡፡

እኚህ አስተሳሰቦቹ በ መዋቅራዊ ችግሮች ላይ ያተኮረ የኢኮኖሚ አተናተን/ሃቲት (Structural economics) እና የ ድህረ-ኬንስ ኢኮኖሚያዊ አተናተን/ሃቲት (Post-Keynesian economics) የሚባሉትን የዛሬ ኢኮኖሚስ ትምህርት ፈርጆቹ ፋና ወጊ መሆናቸዉን ቁልጭ አርገው የሚያሳዩ ናቸው፡፡ ይህ ትንታኔያቸዉም የመንግስት የገንዘብና የ ቀረጥ-ነክ ፖሊሲ ምን መሆን እንዳለበት አጥጋቢ በሆነ መልኩ ለማስረዳት መንገድ ከፍቶላቸዋል፡፡

## 2.1.3 በ ገ/ሕይወት ሞዴል የገንዘብና የቀረጥ-ነክ ፓሊሲ ሁኔታ

በገ/ህይወት ሞዴል ቀረጥ ለመዋለ ንዋይ የሚያስፈልግ ገቢ ማሠባሠቢያ ብቻ ሳይሆን ኢኮኖሚውን በተፈለገበት አቅጣጫ ለመምራት የሚያገለግል የፓሊስ መሣሪያም ጭምር ነው፡፡ ለዚህም ይመስላል የተለያዩ የቀረጥ አይነቶች ላይ (ለምሣሌ የአገር ውስጥ ዕቃ ላይ፣ የወጪ ዕቃ ላይ፣ የቅንጦት ዕቃ ላይ፣ የፍጆታ ዕቃ ላይ ወዘተ) ትንተናቸው ያተኮረው፡፡ ጠቅለል ባለ መልኩም ከቁጥር (10) ዕስከ (13) በተሠጡት ቀመሮች የገ/ህይወት የቀረጥ ነክ መሠረታዊ ሃሳቦች ሊገለፁ ይችላሉ፡፡

$$\text{ቀ}_{\text{አ}} = \text{ተ}_{\text{አ}}(\text{ምዋ}) \quad [10]$$

$$\text{ም} = -\text{የ}(\text{ተ}_{\text{አ}})\ \text{ዉጤት} \quad [11]$$

$$\text{ቀ} = +\text{የ}(\text{መ})\ \text{ዉጤት} \quad [12]$$

$$ቀ_{ዉ} = ተ_{ቅ}(ፍ) + ተ_{ሙ}(መ_{ው}) \quad [13]$$

<u>መግለጫ</u>፡ $ቀ_{አ}$ =ያገር ዉስጥ ቀረጥ ገቢ፤ $ተ_{አ}$ =ያገር ዉስጥ የቀረጥ ምጣኔ፤ ምዋ = ያገር ዉስጥ ምርት በአጠቃላይ ዋጋ (ዋ) ተሰልቶ፤ መ = መዋለ-ነዋይ፤ $ተ_{ቅ}$ = ቅንጦት ዕቃ ላይ የተጣለ የቀረጥ መጣኔ፤ $ተ_{ሙ}$ = ከዉጭ የሚገባ መዋለ-ንዋይ ዕቃ ላይ የተጣለ የቀረጥ ምጣኔ፤ – = አሉታዊ ተፅኖ፤ + = አዎንታዊ ተፅኖ፤ $ተ_{ቅ} > ተ_{ሙ}$ እና $ተ_{ሙ} < 0$ ሲሆን ይችላል፡፡

በቁጥር (10) የተሠጠው ቀመር ምርት ሲያድግ ያገር ውስጥ የቀረጥ ገቢ እንደሚያድግ የሚያሣይ ሲሆን በአንፃሩ የአገር ውስጥ ቀረጥ ምጣኔ ሲያድግ ምርት ሊቀንስ እንደሚችል በቁጥር (11) ተቀምጥዋል፣ በቀመር 11 የተቀመጠዉ ይህ ሁኔታ የገበሬውን ከዕጅ ወደ አፍ የሆነ ኑሮ እንደሚያባብስ ገ/ሕይወት አትተዋል፡፡ የኢንቨስትመንት መጠናከር ግን በቁጥር (12) የተሠጠው ቀመር እንደሚያሣያው ምርታማነትን በመጨመር የመንግስት ገቢን ያዳብራል፡፡ ስለዚህም በቁጥር (11) እና (12) የታዩት የ መንግስት አሉታዊና አዎንታዊ የገቢ ሁኔታ አካሄድ በድምሩ አጠቃላይ የመንግስት ገቢ ወዴት እንደሚያመራ ያሣያሉ ማለት ነው፡፡ በመጨረሻ በወጭ ንግድ ላይ ሊኖር የሚችለውን የቀረጥ ገቢ ሁኔታ አሁንም ካልስኪን በመቅደም በቁጥር (13) ቀመር የተሠጠውን እንደሚመሥል የገ/ሕይወት ሞዴል ያሣያል፡፡ ይህ ቀመር ከውጪ ንግድ የሚገኘው ቀረጥ በቅንጦትና በኢንቨስትመንት ዕቃዎች ላይ ሊጣል እነደሚችል ቢያሳይም በቅንጦት ዕቃ ላይ ቢሆን እንደሚመረጥ ገ/ሕየወት አሳስበዋል፡፡ እንዲያዉም "$ተ_{ሙ}$" ን ከ ዜሮ በታች በማድረግ (ድጎማ በመስጠት) ኢንቨስትመትን ማበራታት እንደሚገባ ጠቁመዋል፡፡

ከዚህ የቀረጥ-ነክ ፓሊስ በተጨማሪ ገ/ህይወት የገንዘብ-ነክ ፓሊሲንም ትንትና ሰጥተዉበታል፡፡ በዚህ ትንተናቸዉ ማንኛውም ልማት፣ ባንክና ገንዘብ ነክ ጉዳዮችን ጨምሮ፣ በዕወቀት ላይ ካለተመሠረት ጉዳቱ እንደሚያይል በተደጋጋሚ ማስገንዘቡን ቀጥለዉታል፡፡ ታዳጊ አገሮች የሠለጠነ የሠው ኃይል ከሌላቸው በባንኮች የተሠበሰበዉን ገንዘብ ተጠቃሚ አይሆንም፡፡ በአንፃሩ የሠለጠነ የሠው ሃይል ያላቸው ያደጉ አገሮች የዚህ ባንክ ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡ ይህንንም ግንዛቤ በሚከተለው ሁኔታ ምሳሌ በመስጠት አጠናክረዉታል፡፡

> በኢትዮጵያ የቆመው የእንግሊዝ ባንክ ከታህሳስ 22 ቀን 1904 ዓ.ም እስክ ታህሳስ 22 ቀን 1905 ዓ.ም ድርስ ያበደረው ገንዘብ ብናስበው1, 220, 850 ብር ይሆናል። ከዚሁም የኢትዮጵያ ህዝብ የተበደረው 50000 ብር በላይ አይሆንም ይሆናል። የቀረው ግን 1, 170, 850 ብር የውጪ ሃገር ሰዎች ተበድረው ሰሩበት።(ገጽ 126)

ገ/ሕይወት ስለ ገንዘብ ፓሊሲዎች ሲተነትኑ እንደ አንድ ጥሩ የፓሊስ መሣሪያ አድርገዉ የሚገልፁት ባንኮች የሚያስከፍሉትን የወለድ መጠን ነው፡፡ ለገ/ሕይወት ልማት/ዕድገት የባንክና የመገናኛ አውታሮችን ስለሚያስፋፉ፡ መበደር ከባድ አይሆንም (ምክንያቱም ንግድ ይስፋፋል፣ ሰዎች ገንዘባቸውን ከማስቀመጥ ይሰሩበታል በመሆኑም የገንዘብ መጠን ኢኮኖሚዉ ውስጥ

ይጨምራል)፡፡ በዚህም ምክንያት ባንኮች የሚያስከፍሉት የወለድ መጠን ዝቅ ይላል፡፡ ስለሆነም ለገ/ሕይወት የወለድ መጠንና የአገር ዕድገት ተቃራኒ የጉዞ መስመር ይከተለሉ፡፡ ይህም ማለት ያደጉ አገሮች የባንኮች የወለድ መጠን ዝቅ ያለ ሲሆን ያላደገ አገር ባንኮች የወለደ መጠን ግን ከፍ ያለ ነው፡፡

ሌላው ገ/ህይወት ያነሱት ገንዘብ ነክ ጉዳይ የባንኮችን ገንዘብ የመፍጠር አቅምና መንግስት ግሽበትን ተጠቅሞ ህዝቡን በተዘዋዋሪ ቀረጥ ማስከፈል እንደሚችል ማተታቸዉ ነው፡፡ ይህንንም ሁኔታ ቢጊዜው የነበረውን የአቢሲንያ ባንክ አሃዝ በመጠቀም አብራርተዉታል፡፡ ዕውቅት ለሌለው ህዝብ ባንኮች የሚፈጥሩት ገንዘብ ከጥቅሙ ጉዳቱ እንደሚያመዝን ከማተታቸዉም በላይ፣ መንግስትም ግሽበትን ተጠቅሞ ገንዘብ መሠብሰቡ ምንም እንኩዋን ለመንግስት ቀላል ግብር የመሰብሰቢያ ዘዴ ቢሆንም ግልፅነትና ተጠያቂነት የሌለው አሠረር ስለሆነ ገ/ህይወት ተቃዉመዉታል (እንዳዉም ይህንን ሃሳብ መፃፍ ቀፎአቸዉ ነበር)፡፡ ይህ አይነቱ የመንግስት አካሄድ የሠረተኛውን ህዝብ የመግዛት አቅም እንደሚያመንምንና በዚህም ሠራተኛው እንደሚጎዳ ገልፀዉታል፡፡

በጨረሻም የገ/ሕየወት የገንዘብ ነክ ትንታኔ የገንዘብ ፍላጎት ቀመር ላይ የተኮረ ነበር፡፡ በጊዜው በኢኮኖሚው ዉሰጥ የነበረውን የሸርፈረፊ ገንዘቦች ዕጥረት በመጥቀስ ይህንን ክፍተት ለመዝጋት የገንዘብ አቅርቦቱ ከአውሮፓ በመምጣት ከ ኢትዮጵያ ትርፍ አጋብሶ ሊሄድ እንደሚችል ስጋታቸዉን ገልፀዋል፡፡ ይህም የሆነው በጊዜው የነበረው ገንዘብ የብር ወይም ወርቅ በመሆኑ ነው፡፡ ይህንን አደጋም ለመቀነስ የሚከተሉትን የፓሊስ አቅጣዎች መንግስት እንዲከተል ጠቁመዋል፡፡

i. 1ኛ/ መንግስት የራሱን ገንዘብ ከበቂ ሽርፍራፊ ጋር እንዲያትም
ii. 2ኛ/ የገንዘብ ፍላጎትን በማጥናት ተመጣጣኝ አቅርቦት እንዲያደርግ፡፡ ይህንንም ሥራ መንግስት ብቻ እንዲሠራው፡፡
iii. 3ኛ በተለያዩ ከተሞች ማህል ያለውን የዋጋ ልዩነት ለማጥበብና በትንሽ ገንዘብ ብዙ ንግድ ለማካሄድ እንዲችል (የአንድዋን ብር አማካይ ዝዉዉር እናም የምታስተናግደዉን የንግድ መጠን በመጨመር ) መንግስት መሠረት ልማቶችን እንዲያስፋፋ፡፡
iv. 4ኛ የገንዘቡን ሕጋዊ ተቀባይነት በመደንገግ የግድ ብር ወይም ወርቅ መሆኑን በሂደት መቀነስ፡፡

እኚህ የገ/ሕይወት የፓሊስ አቅጣጫዎችን ልዩ የሚያደርጋቸው የገንዘብ-ነክ ፓሊሲዎች ሰፋ ባለ ልማታዊ ቅኝት ስር የተወጠኑ መሆናቸው ነው፡፡ ለዘህም በጣም ግልፁ ምሳሌ በቁጥር 3 የተሠጠው የፓሊስ አቅጣጫ ነው፡፡

## 2.2 ውጫዊ የልማት መሰናክሎች

በነጋድራስ ሞዴል ‘ውጫዊ የልማት መሰናክሎች’ ያልኳቸው ኢትዮጵያ በውጪ ንግድ በኩል ያላትን ግንኙነት መሰረት ያደረገዉን አተናተናቸዉ ነው፡፡ ለነገሩ አስተሳሰቡ ባጠቃላይ ላደገና ላላደገ አገር ንግድ ልውውጥ መገለጫ ሊሆን ይችላል፡፡ በዚህ ርዕሰ ጉዳይ የነጋድራስ መሰረታዊ ሀሳብ የሚያጠነጥነው በተለያየ የዕድገት ደረጃ ላይ ባሉ ሁለት ሃገሮች ነው፤ ለምሳሌ አውሮፓና ኢትዮጵያ ሲነግዱ ያላደገው አገር እንደሚጎዳ ማስረዳቱ ላይ ነው፡፡ ሊዚህ ደግሞ መሰረታዊው ምክንያት ያላደገው አገር ምርት ብዙ ዕውቀት የሌለበት ጥሬ ዕቃ እና የትራንስፖርት ወጪው ትልቅ ሲሆን፤ ያደገው አገር ዕቃ ደግሞ የተቃራኒውን ይዘት ይይዛል፡፡ ይህ ደግሞ ላልተመጣጠነ የንግድ ልውውጥ ብሎም ላላደገው አገር ድህነት መዳረግ ምክንያት ይሆናል፡፡ ይህንንም ሲያብራሩ፡

> ... እንግዲህ ለአንዱ ኮሮጆ አቡጀዲ እስከ ሶስት በሬ ይሰጥበታል፡፡ ስለምን በሬው በሽታ እንዳይገለው፣ አውሬው እንዳይበላው ከመጠበቅና ወደ ገበያ ከመውሰድ በቀር ሌላ የሰው ድካምና እውቀት አላለፈበትም፡፡ ያቡጀዲው ጥጥ ግን አቡጀዲ እስከሚሆን ድረስ በብዙ ሰዎች እጅና በብዙ መኪናዎች ውስጥ ገብቶ ተደክሞበታለ፡፡ በፈረንጅ አገር በሬውም ቢሆን ብዙ ዋጋ ያወጣል፡፡ ስለምን ህዝቡ በዝቶ ሀገሩ ጠባብ ስለሆነ በሬው በልቶ የሚያድገው ሳር ተዘርቶ፣ ታጭዶ፡ ተከምሮ ነው፡፡ ቤቱም የሚሰራ በስንት ድካም ነው፡፡ ...ስለዚህም ከኤሮጳ አገር ለሚመጣልን ነገር ሁሉ ዋጋ የምንሰጠው ስለ ስራው ነው እንጂ ስለ ብዛቱ አደለም፡፡ ያቡጀዲ ጥጥ እንጂ ስራው ወደ አገራችን መጥቶ ፍግ እንዳይሆን የታወቀ ነው፡፡ ...እንግዲህ እውቀት አንሰሶት የሚያስፈልገውን ነገር ሁሉ በገዛ እጁ ለመስራት የማይችል ህዝብ የሚያገኘው ጉዳት ምን እንደሆነ ከተረዳነው ዘንድ፣ ይህንን ጉዳትና ባርነት አጥፍቶ ወደ ሀብትና ወደ አርነት የሚወስደውን መንገድ አንመልከት፡፡ (ገጽ 71)

ያላደገው አገር ጥቅም ካደገው አገር ጥቅም ጋር ሲነፃፀር በጣም የማሽቆልቆል ዝንባሌ ይኖረዋል፡፡ የኢኮኖሚ ተንታኞች ይህን ሃሳብ (ዝንባሌ) ‘የፕሬሽብሽ-ሲንገር’ አስተሳሰብ ወይም ሃይፓተስስ ይሉታል፡፡ እኔ ግን የነጋድራስ ገ/ህይወት አስተሳሰብ (ሃይፖተስስ) ብዮዋለሁ ምክንያቱም እሳቸው 50 ዓመት ከፕሬብሽና ከሲንገር በፊት ቀድመው ስላወቁትና ስለፃፉት ነው፡፡ ጠቅለል ባለ መልኩ የገ/ህይወት ዉጪያዊ የልማት መሰናክሎች በቁጥር [14] በተሰጠዉ ቀመር ሊገለፁ ይችላሉ፡

$$(\text{ወጪ.ን})_{\text{ኢ}} = (\text{ግ})_{\text{አ}} + \text{ት}_{\text{አ}} = (\text{ገቢ.ን})_{\text{ኢ}} \qquad [14]$$

<u>መግለጫ</u>፡ $(\text{ወጪ.ን})_{\text{ኢ}}$=(የኢትዮጵያ) ወጪ ንግድ፤ $(\text{ግ})_{\text{አ}}$=የግባዐት ወጪ (በአዉሮፓ)፤ $\text{ት}_{\text{አ}}$= ትርፍ (በአዉሮፓ)፤$(\text{ገቢ.ን})_{\text{ኢ}}$ = ገቢ ንግድ (የኢትዮጵያ) ኢ= ኢትዮጵያ አ= አዉሮፓ

ይህ ቀመር በአትዮጵያና በአወሮፓ መሃል ያለው የገቢና ወጪ ንግድ ሚዛን የተመጣጠነ እንደሆነ ያሣያል፡፡ ሆኖም ግን በ ገ/ሕይወት ሞዴል ኢትዮጵያ ጥሬ ዕቃ፣ አውሮፓ ግን የተፈበረከ ዕቃ ስለሚልኩ፣ ኢትዮጵያ ትጎዳለች፡፡ ይህም የሚሆነው ቀደም ብዬ እንደጠቀስኩት

በሁለት ምክንያት ነው፡፡ አንደኛው የተፈበረከ ዕቃ የትራንስፖርት ወጪዉ ትንሽ ሲሆን ጥሬ ዕቃ ግን የትራንስፖርት ወጪዉ ከፍ ይላል፡፡ በሁለተኛ ደረጃ የተፈበረከ ዕቃ ብዙ ዕወቀት ስለፈሰሰበት ዉድ ሲሆን ጥሬ ዕቃ ግን ብዙ ዕወቀት ስላልፈሰሰበት በአንፃራዊነት ሲታይ ርካሽ ይሆናል፡፡ በጊዜ ብዛትም ምድሪቱ ለግማብን ጥሬ ዕቃዉን ብቻ ሳይሆን የምንበላዉንም ማምረት ስለማንችል የእኛም የልጅ ልጆቻችንም ዕጣ ወደ አደጉት አገር መሰደድ እነደሚሆን አትተዉት ነበር፡፡ ይህ ንድፈ-ሃሣባዊ አካሄድ በመስኩ ቀደምት ከሚባሉት ከነ ሲንገርና ፕሬብሽ ሀሳብ ቀዳሚ ብቻ ሳይሆን ከነሱ የተለየ ጎንም አለዉ፡፡

በመጨረሻም ነጋድራስ ይህንን ውጫዊ የልማት መሰናክል ያልኩትን ክፍል ለማጠቃለል አለማቀፍ ገንዘብ ነክ ጉዳዮችን ይዳስሳሉ፡፡ በዚህ ትንታኔያቸዉ ካፒታል (ገንዘብ) ከአገር አገር የሚዞረው የተሻለ ትርፍ ፍለጋ መሆኑን በመተንተን በኢኮኖሚክስ ጥናቶች ውስጥ ገንኖ የታወቀውን የፕሮፌሰር መንደልና ፍላሚንግ ሞዴል (ምንም እንኳ የእንገሊዙ ሊቅ ዴቪድ ሪካርዶና ማርክስ ቀደም ብለዉ ያሉት ጉዳይ ቢሆንም) ነጋድራስ ቀድመዉ ጠቁመዉታል፡፡ እነ መንደል ይህንን ሃሳብ አገኙ የተባለዉ ከ50 ዓመት በኋላ በ 1960ዎቹ ነበር፡፡

እንደ ገ/ህይወት አተናተን ይህ አይነቱ ትርፍ ፈላጊ ካፒታል ተጠናክሮ እንዲመጣ በጊዘው ያለው የሥራ ክፍፍል ደረጃ ዋንኛው ምክንያት ሲሆን፣ ይህ ግን ያገር ውስጥ ኢንደስትሪ እንዳያድግ ዕንቅፋት እደሚፈጥር አትተዋል፡፡ ይህ ትንተና ከመሠረት ልማት ግንባታ ጋር የተቆራኘ መሆኑን የገ/ህይወት ሞዴል ያሣያል፡፡ በገ/ህይወት አስተሳሰብ ዕወቀት በሌለው ህብረተሰብ የመሠረት ልማት መስፋፋት ካፒታል ወደ አገሩ ዘልቆ ዕንዲገባ በማድረግ የአገር ውስጥ ዕደ-ጥበባትን በማኮስስ ና የብድር ጫናን በማጠናከር ያለደገውን አገር በአደገው አገር የመበዝበዝ ሁኔታ ያጠናክራል፡፡ ከዚህ ትንትኔ በመነሣት ያገር ውስጥ ምርትን በማጠናከር ራስን በራስ የመቻል አላማ ሊኖር እነደሚገባና ይህም የሚከተሉትን የፓሊስ አቅጣጫዎች በመከተል ሊተገበር እንደሚገባ አስረድተዋል፡፡

i. 1ኛ ተገቢ የሆኑ የቀረጥ ፓሊስ፡- የአገር ዉስጥ የአንዱስትሪ ምርትን የሚያበረታታና ከወጪ የሚመጠትን ምርቶች የሚገድብ
ii. 2ኛ የመሠረት -ልማት ግንባታ ማካሄድ
iii. 3ኛ የመዋለ ንዋይ ፍሰትን በአግባቡ በመቆጣጠር ማበረታታት

የመጨረሻውን ነጥብ ሲያጠናክሩም ገ/ሕየወት የሚከተለዉን ብለወል፣

> ምቼም የኢትዮጵያ ህዝብ የሚያስፈልገውን እቃ ሁሉ የሚገዛው ከውጭ አገር ሰዎች ነው። ሰራተኞቹ ያሉበት ቦታ ሩቅ ስለሆነ ግን እቃውን አገኛለሁ ሲል ብዙ ትርፍ ድካም ይሄድበታል። ጥቅሙ ን የሚያገኙት ግን ነጋዴዎች ናቸው። ስለዚህ የውጪ አገር ሰዎች ድካማችንን መውሰዳቸው ላይቀር አጠገባችን እየሰሩ ቢወስዱት ይሻላል። (ገጽ 98)

## 2.3 የገ/ህይወት ሞዴል በዘመኑ ከነበሩ ኢትዮጵያዊ ምሁራን የኢኮኖሚ አስተሳሰብ ጋር ያለዉ ዝምድናና የጊዜ ሂደት በትነተናዉ ላይ ያለዉ ተጽኖ

ሁለት የዘመኑ ምሁራን ከገ/ህይወት ሥራ ጋር ባላቸው ቁርኝነት ሊጠቀሱ የሚገባ ነው፡፡ እኚህም ብለታ ደሬሳ አመንቴና አቶ ሚካኤል ተሰማ ናቸው፡፡ እኚህ ምሁራን በዘመኑ ዕውቅ በነበረው የ “ብርሃንና ሠላም” ጋዜጣ ላይ ከኢትዮጵያ የዕድገት ችግር ጋር የተያያዙ ብዙ ቁም ነገሮችን ተንትነዋል፡፡ ሆኖም እዚህ የጠቃቀስኩት ከገ/ህይወት ጋር የሚያያዘውን ብቻ ነው፡፡

ከብላታ ደሬሳ ብንጀምር ከጃፓን ልምድ በመማር በኢትዮጵያ ልማት ለማምጣት ዕውቀት (ትምህርት) ማስፋፋት ቁልፍ እንደሆነ ያብራራሉ፡፡ ይህ ግን ዘላቂነት እንዲኖረው ተቋማትና ሥርዐት መዘርጋት ወሣኝ እንደሆኑ ተንትነዋል፡፡ ለዕውቀት የሠጡት ቦታ በገ/ህይወትም የተተኮረበት ሲሆን ገ/ህይወትም ሥርዐት ያላት ትንሽ አገር ሥርዐት ከሌለው ትልቅ አገር ሙያ ትሠራለች፣ ሀይል ሥርዐት እነጂ የሰራዊት ብዛት አይደለም ሲሉ ይህንንኑ የብለታ ደሬሳ ሃሳብ፡ ተንትነዉት ነበር፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ሁለቱም ለመሠረት ልማት መስፋፋት የሠጡት ትኩረት፤ ያ ደግሞ በዕቃዎች ዋጋና በገንዘብ አጠቃቀም ላይ ያለው ተፅኖ ሁለቱም የሚገናኙበት ጉዳይ ነው፡፡ ብለታ ስለ አንፃራዊው የኢትዮጵያ የወጪ ንግድ ጥቅም በተለይም ከአውሮፓው አቻው ጋር ሲታይ የማሽቆልቁሉ አዝማሚያ ላይ ያረጉት አሃዛዊ ትንታኔም በገ/ህይወት ሃሳብና ቀደምት ተመሳሳይ ስራ ላይ ተንተርሰው የሠሩት ይመስላል፡፡

ከብላታ ደሬሳ በተጨማሪ የገ/ህይወት ሃሳብ ከሚካኤል ተስማም የ “ብርሃንና ሠላም” ትንተና ጋር ይያያዛል፡፡ ሚካኤልና ገ/ህይወት ለዕወቅት ያላቸው ትኩረትና ስንፍናን በማስወገድ ላይ ያላቸዉ አመለካከት ተመሳሳይ ነዉ ፡፡ በሌሎች አቅጣጫ ግን ሰፋ ያለ ልዩነት አላቸው፡፡ ለምሣሌም ሚካኤል ዓለም-አቀፍ ንግድ ለኢትዮጵያ ጠቃሚ መሆኑን ሲከራከሩ ገ/ህይወት በታቀራኒው፡ የቆሙ ነበር፡፡ ገ/ህይወት የገቢ ሥርጭት ሁኔታ ሲያሳስባቸዉ ሚካኤል ግን ይህ ፍታዊ የክፍያ ሥርዓት ነው፡ ይላሉ፡፡ በአጠቃላይ ሲታይ፡ ሚካኤል የኢኮኖሚ ፅንፀ ሃሳቦችን በህዝቡ ውስጥ በሚገባው ቋንቋ ለማስረፅ ቢጥሩም (ለመጀመሪያ ጊዜ የኢኮነሚክስ አሰተሳሰቦችን በስዕላዊ ሰንጠረዥ ባማርኛ በመስራት ጭምር)፣ ከኢትያጵ ሁኔታ ገር ለማዛመድና ጠለቅ ብለው ለመተንተን እነደ ገ/ሕይወት የደከሙ አይመስልም፡፡

ይህ ከላይ የጠቀሰኩት ገ/ሕይወት በዘመኑ ከነበሩ ኢትዮጵያዊ የኢኮኖሚ ተንታኞች ጋር ያለው ቁርኝት መሠረታዊ ገፅታ ሲሆን ፅሁፌን ከማጠቃላሌ በፊት ግን የገ/ሕይወት አስተሳሰብ ከጊዜ ሂደት አንፃር ሲታይ ምን መልክ እንደሚይዝ ለመጠቆም እወዳለሁ፡፡ እስካሁን ባየነው የገ/ህይወት ሞዴል ገለጻዬ ውስጥ ዛሬ ወይም ዘንድሮ የሆነው ነገር ነገና ተነገ ወዲያ ወይም የሚቀጥለዉ ዐመት ሊያመጣ የሚችልውን ተፅኖ (ፈረንጆቹ ዳይናሚክስ የሚሉትን፤ በዐማርኛ “ተገሳጋሽነት” ልንለዉ የምንችለዉ) ትኩረት አልሰጠሁትም ነበር፡፡ ዕውነታዉ ግን የገ/ሕይወት ሥራ  የጊዜ ሂደት በልማት ላይ ያለውን ተፅኖ (ተገሳጋሽነትን) በአንክሮ ያጤነ ነው፡፡ ሙሉዕ በሆነው የገ/ሕይወት ሞዴል የዛሬው ግጭት በሰው ሃይል ሀብት ላይ ያለው አሉታዊ ተፅኖ ዛሬ

ላይ ብቻ ተወስኖ የሚቀር ሳይሆን መጪውን ጊዜ/አመታት ያካትታል፡፡ በተመሣሣዩም የዛሬው የንግድ ልውውጥ መዛባት ተፅኖ ዛሬ ላይ ብቻ ሳይወሰን ለሚቀጥሉት አመታትም የሚዘልቅ ነው፡፡ የነዚህ ድምር ውጤት (የ ኢኮኖሚዉ ተገሳጋሽነት) የዛሬውን ምርታማነትና ምርት ለይ ብቻ ተፅኖ መሳደር ብቻ ሳይሆን የመጪው (የወደፊቱ) ጊዜ ምርትና ምርታማነትም ላይ አሉታዊ ተፅኖ ይኖረለዋል፡፡ ስለሆነም የመፍትሔ ሃሳብ ፍለጋው ዘመን ተሻጋሪ መሆን አለበት ማለት ነው፡፡ ይህ አስተሳሰብ ከአንዱ ተማሪዬ (ከ አብረሃም አበበ) ጋር በቅርቡ እንዳደረግነዉ ጠለቅ ባለ የሂሳብ ቀመር ሲሠራ የገ/ሕይወትን የጠለቀ አስተሳሰብ ጥርት አድርጎ ያሳያል፡፡ በተጨማሪም ገ/ህይወት ያነሱትን መሰረታዊ የልማት ችግሮች አጥጋቢ መፍትሔ ለመሰጠት መንገዱን ወለል አድርጎ ይከፍትልናል፡፡ አጥርቶ ማየት ደግሞ የመፍተሄ ፍለጋ ሀሁ ነዉ፡፡

# III፡ ማጠቃለያ

ለማጠቃለል ያህል፣ በዚህ አጭር ፅሁፌ አንባቢ የነጋድራስ ስራ ምን ያህል ጥልቅና ድንቅ እንደሆነ እንደሚረዳልኝ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ በተለይም ደግሞ ‘ልማታዊ የኢኮኖሚ ትንታኔ” በሚባለው የኢኮኖሚክስ ትምህርት ፈርጅ ድንቅ የተባሉትን ግኝቶች ነጋድራስ ግኝቶቹ ተገኙ ከተባለበት 40 ና 50 አመት በፊት እንደጻፏቸዉ አንባቢው ይገነዘባል፡፡

በሁለተኛ ደረጃ የነጋድራስ አስተሳሰቦች ድሮ ተሰርተዉ ታሪክ ሆነው የሚቀሩ ሰነዶች በቻ እንዳልሆኑ ለማሣየት ሞክሪያለሁ፡፡ ነጋድራስ የዛሬ መቶ አመት ገደማ የኢትዮጵያ መሰረታዊ ችግሮች ብለዉ ምሁራዊ ትንታኔና የፖሊስ አቅጣጫን ያሳዩባቸው ጉዳዮች በሚያሳዝንና በሚያሳፍር መልኩ ዛሬም ከእኛ ጋር ያሉ፤ ዛሬም ምክራቸዉን ያልተጠቀምንበት መሆኑ ነው፡፡ እንግዲህ ይሄንንም ሃሳብ በተቻለኝ አቅም ለማሳየት ሞክሬያለሁ፡፡

በመጨረሻም የነጋድራስ ሃሳቦች የረቀቁና የመጠቁ ስለሆኑ ለብዙ ምርምሮችና የፖሊስ ሃሳቦች በር ከፋች መሆናቸውን ላሰምርበት እፈልጋለሁ፡፡ ተመራማሪዎችና ፖሊሲ አዉጪዎች ይህንን አቅጣጫ ቢከተሉና የፖሊስ አቅጣጫቸውንም በዚህ ተንተርሰው ቢያዩ ዛሬም ፍሬያማ ሥራ ሊሠሩበት እነደሚችሉ በማስገነዝብ ጽሁፌን በዚሁ አጠቃልላለሁ፡፡

## ዋቢ ጽሁፎች

Alemayehu Geda (2011) 'Does Conflict Explains Ethiopian Backwardness? Yes and Signficantly' in Alemayehu Geda. *Readings on Ethiopian Economy.* Addis Ababa:Addis Ababa University Press.

Alemayehu Geda (2002) 'The Gebre-Hiwot Model: A Pioneer African (Ethiopian) Development Macroeconomist' *Ethiopian Journal of Development Research,* 24(1): 1-27.

Alemayehu Geda (2005) 'Ethiopian Macroeconomic Modelling in Historical Perspective: Bringing Gebre-Hiwot and his Contemporaries in Ethiopia's' Macroeconomic Realm, *Journal of Northeast African Studies,* 10(1):145-168.

Alemayehu Geda and Abraham Abebe (2012, forthcoming) 'The Dynamics of Gebre-Hiwot Model: A Dynamic Modelling of Current and Early 20th Century Ethiopia's Development Thinking, *Journal of Northeast African Studies,* forthcoming.

Chang, Ha-Joon (2002). *Kickin Away The Ladder: Development Strategy in Historical Perspective*. London: Anthem Press.

Messay Kebede (2006) 'Gebrehiwot Baykedagne, Eurcentrism, and the Decentering of Ethiopia', *Journal of Black Studies,* 36(6): 815-832..

ነጋድራስ ገበረ ሕይወት ባይከዳኝ (2002) *የነጋድራስ ገበረ ሕይወት ስራዎች፡፡* አዲስ አባባ፣ አዲስ አባባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ (ነባር ምርጥ መጻሕፈት ሐትመት ፕረሮግራም)፡፡

አለቃ ታዬ (1914) *የኢተዮጵያ ህዝብ ታሪክ፡፡* አዲስ አበባ፣ሴንትራል ማተሚያ ቤት ፡፡

አየለ ዘዉገ (1973) የ ነጋድራስ ገበረ ሕይወት ባይከዳኝ የ ፖለቲካ ኢኮኖሚ አሰተሳሰብ፤ መሰከረም መጽሄት፤ ቀጽ ፲፡ ቁጥር 3 ና 5.

Weber, Max (1930). *The Protestant Ethic and the Spirit of Capitalism.* London/New York: Routledge.

# LIST OF IAES WORKING PAPERS

| No | Authors | Title | No and Year |
|---|---|---|---|
| | | | |
| | | 2011 | |
| 1 | Alemayehu Geda and Kibrom Tafere | The Galloping Inflation in Ethiopia: A Cautionary Tale for Aspiring 'Developmental States' in Africa | WP A01_2011 |
| 2 | Alemayehu Geda, Kibrom Tafere and Melekt Amedu | Remittance and Remittance Service Providers in Ethiopia | WP A02_2011 |
| 3 | Alemayehu Geda and Abrham Abebe | A Dynamic Modelling of Gebre-Hiwot Ideas: 0f Early 20$^{th}$ Century Ethiopia's Development Problems | WP A03_2011 |
| 4 | Alemayehu Geda and Atenafu G. Meskel | Impact of China-Africa Investment Relations: Case Study of Ethiopia | WP A04_2011 |
| 5 | Alemayehu Geda | Economic Ideas of Gebre-Hiwot Baykadagn (A great early 20th[1924] century thinkers, in AMHARIC) | WP A05_2011 |